# ዋጋ ያለው የሆነ

ምክንያቱም ሕይወት

## ዋጋ ያለው ነው

( በመርጃ ኩቡ ላይ ያሉትን የማመልከቻ ቀስቶችን ተመልከት የማስተማሪያ ስዕሉን ወዴት መክፈት እናዳለብህ ይረዱሃል)

## 1 ⬅ ➡ የሰው ሕይወት ዋጋ ምንድነው?



- እነዚህ ሰዎች የሚወክሉት በአለም ሁሉ የሚገኙትን በአለባበሳቸው ፤ በአኗኗራቸው ፤ በባህላቸው የተለያዩ ህዝቦችን ነው።
- ሁላቸውም ለራሳቸው የሰጡት ዋጋ ግምት አላቸው፤ (አንዱን አመልክትና ጠይቅ)። የዚህች ሴት አባት ሊሞትባት ቢሆን እርሷ ህይወቱን ለማዳን ምን ታደርጋነች? ወይም የዚህኛው ሰው ወንድም በከባድ ችግር ውስጥ ቢሆን እርሱን ለማዳን ምን አይነት እርምጃ ሊወስድ ይችላል?
- እያንዳንዱ የምታዩአቸው ሰዎች የሚወዱትን ሰው ህይወት ለማትረፍ ያላቸውን ነገር ሁሉ ይሰጣሉ ምክንያቱም የሰው ሁሉ ህይወት የዋጋ ግምት ያለው ነውና።
- ሌላውና እኛ ሁላችንም በጋራ ያለን የምንመኘውና የምናደርገው ተመሳሳዩን ነው።

## 2 ⬅ ➡ በሕይወታችን ሁላችንም የምንፈልገው ምንድነው?



- የኢኮኖሚ ለውጥ
  (ወደ ገንዘብ አመልክት)- የተሻለ ገንዘብ ለማግኘት/ ምን መስራት ትፈልጋለህ? ምን ታደርግበታለህ? በገንዘቡ ምናልባትም የምንፈልጋቸውን ነገሮች ለመግዛት እንሞክራለን። ለምሳሌ ልብስ መግዛት ፣ አዲስ ስልክ መግዛት ወይም ደግሞ ያገኘከውን ገንዘብ ለትምህርት ቤት ክፍያ ልንጠቀም እንችላለን።
- ትምህርት
  (ወደ መጽሐፍና ልጅ አመልክት)- ትምህርት ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድነው?

- ልጆቻችን በጣም ጠንክረው እንዲማሩ እንፈልጋለን ምክንያቱም የወደፊቱ ህይወታቸው የተሻለ እንዲሆን የተሻለ ስራ እንዲኖራቸውና የተሻለ ገንዘብ እንዲያገኙ ስለምንፈልግ ነው።

- እኩልነት

- የምንሰራው የተሻለ ትምህርት ወይም ገንዘብ ለማግኘት ሲሆን ማን መሆናችንንና ከየት መምጣታችን ወይም የት መኖራችን ለማሳየት ነው። (በመሀል ወደሚገኙት ሦስት ሰዎች አመልክት) የተከበርን ሆነን መታየትና የምንከበር ልንሆን እንወዳለን፤

## 3 ⬅ ➡ የምናከብራቸው ሰዎች እነማን ናቸው?



- የኃይማኖት መሪዎች ፡-
  እነዚህም ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ሰላም እንደሚኖረንና ህብረት እንደምንፈጥር
  እንደሚያስተምሩን
  ተስፋ እናደርጋለን
- ባሎች /ወንድ ፍቅረኞቻችን
  በአክብሮት እና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ፍቅራቸውን ይገልጹልናል
- ቤተሰብና ጓደኞችቻችን፡-
  እናቶች፣ አክስቶች፣ሌሎች ጎረቤቶቻችን ታዳጊዎች በሆንን ጊዜ ሊጠነቀቁልን ይጥራሉ
- ኃብታም የሆኑ ባለኃብቶች
- እነኚህ ለህይወታችን እድገት እንዲሆንልን የምንፈልጋቸውን ገንዘብ፣ ደረጃና አክብሮት፤ በበቂ ሁኔታ እንዲኖረን ያደርጋሉ።

## 4 እነዚህ ልጆች ከቤት የሚወጡት ለምንድነው? የሚሄዱትስ ወዴት ነው?



- ኃብታም የሆነ ነጋዴ ሰው
  ለቤተሰባቸው ትንሽ ገንዘብ ይሰጣቸውና ቃል ገብቶ ልጆቹን ወደ ሌላ ሀገር እንደሚወስዳቸውና እዚያም እስፖርት እና ደግሞም ትንሽ ሥራ እንደሚሰሩለት እንዲሁም እርሱ በየወሩ የሰሩበትን ገንዘብ ለቤተሰባቸው እንደሚልክላቸው ተስፋ ሰጥቶ ተሰናብተው እንዲሄዱ ያደርጋል (የስንብት እጅ እንዲያወዛውዙ አድርግ)
- የኃይማኖት መሪዎች
  ልጆቹን ወደ ከተማ ለትምህርት እንዲወስዱ ይሰጣሉ (በቀኝ እጅ በኩል ያለውን ቤተሰብ የመደገፍ ምስል አመልክት) ቤተሰቡ ልጆቻቸው ከቤት ሲወጡ ኃዘን ይሰማቸዋል ሆኖም ግን ልጆቹ የተሻለ ትምህርት ለማግኘት ወደ ከተማ ስለሚሄዱ ይደሰታሉ፡፡
- በከተማ የምትኖረው አክስት
  ለዚህች ልጅ በጓደኛዋ ምግብ ቤት እንድትሰራ ሥራ ትፈልግላታለች /ታስገባታለች/ (በመስኮት በኩል ወዳለችውና ወደቆመችው መኪና ጠቁም) ወደፊት በዚህ ሥራ ብዙ ገንዘብ ስለምታገኚ ያን ያክል አስገራሚ ኃብት ትሰበስቢአለሽ ትላታለች
- ሁሉም ሰዎች ይህንን ዕድል የመረጡበት ምክንያትና ልጆቹ ከቤት የወጡበት ምክንያት በአንድ በሚያምኑት ሰው የተሰጣቸው ጥሩ ተስፋ ስላጓጓቸው ነው፡፡ ( በጉልበት ወደተወሰደችው ልጅ አመልክት) ነገር ግን ይኸችኛዋ ልጅ በግድ ስለተወሰደች የት እንዳለችና የት እንደተወሰደች ማንም ሰው አያውቅም፡፡
- እነዚህ ቤተሰቦች የሚያምኑት ትክክለኛ ምርጫ ማድረጋቸውን ነው
- በእነርሱ አስተሳሰብ ልጆቹ የትም ሆነ የት ከእነርሱ ቤት ግን በተሻለ ቦታ እንዳሉ ያስባሉ፤ ስለሆነም በእነርሱ እምነት ሌላ ምንም አማራጭ እንደሌላቸው ነው፡፡

## 5 እውነቱ ምንድነው? ማታለያውስ?



- ባሎች እና ወንድ የሴት ጓደኞች ከሚወዷቸው ጋር ሰላማዊ ኑሮ ለማድረግ አብረው ይሰራሉ ጥሩ ሰዎች ስለሆኑም ሚስቶቻቸውን እና ሴት ጓደኞቻቸውን አይጎዱም፡፡
  ነገር ግን አንድ አንድ ባሎች ወይም ወንድ ጓደኛ ሚስቱ ወይም ሴት ጓደኛው ለገንዘብ ወይም ለጥቅም ብሎ ከሌላ ሰው ጋር የግብረስጋ ግንኙነት እንድታደርግ ካስገደዳት ይህ ሰው ሰላማዊ ሰው አይደለም፡፡
- ከተለያዩ አካባቢ የኃይማኖት መሪዎች ወደ ቤትህ ይመጡ ይሆናል ከአንተ ጋር ይኖሩና ቋንቋህንም ይናገሩ ይሆናል፤ ከእግዚአብሔርም ጋር እንዴት በሰላም መኖር እንደምትችል ያስተምሩሃል፤ እነዚህ ሰዎች ጥሩ ሰዎች ናቸው፡፡
  አንዳንድ ጊዜ የኃይማኖት መሪዎች የሚለብሱትን ልብስ የለበሱ ሰዎች ነገር ግን እግዚአብሔርን የማያውቁ ወደ አንተ ሊመጡ ይችላሉ ፡፡ እንዲሁም ገንዘብ ሊሰጡህና ልጅህን ከቤት ሊያወጡ የሚፈልጉ ከሆኑ ሰላማዊ አይደሉም
- አንዳንድ ጊዜ ኃብታም ሰዎች ወደ ሰፈርህ መጥተው መልካም ስራዎችን ሊሰሩ ይችላሉ ለምሳሌ ትምህርት ቤት ሊገነቡላችህ ይችላሉ ወይም የህክምና መገልገያ ፤ ወይም ደግሞ ለቤተሰባችሁ የሚጠቅም ንፁህ ውኃ ሊያወጡላችሁ ይችላሉ፡ እነዚህ መልካም ሰዎች ናቸው፡፡
  ነገር ግን እነዚህ ኃብታም ሰዎች ገንዘብ ሰጥተንህ ልጅህን ወደሌላ ስፍራ እንውሰድ ቢሉህ ጤነኛና መልካም አይደሉም፡፡
- ጎረቤህ ፤ ሴቶች አክስቶች እና አንዳንድ እናቶችም ልጆቻችሁ እንዲማሩ ማድረጋቸው ወይም ጥሩ ስራ እዲያገኙ መርዳታቸ በጣም ጥሩ ምግባር ነው፤
  ነገር ግን አንዲት ሴት ወይም አንተ የምታውቀው ማንኛውም ሰው ለልጅህ ጥሩ ስራ ወይም የትምህርት እድል አግኝተንላታል፣ ስለዚህ ወደ
  ሌላ ቦታ እንዲሔድ የትራንስፖርቱን ወጪ እኛ እንሸፍናለን እንዲሁም የሚያስፈልገውን መታወቂያ እኛ እናዘጋጃለን ቢሉህ ጤነኛ ሴቶች አይደለም፡፡

## 6 ልጆች አሁን የት ናቸው?



- ልናምናቸው የምናስባቸው ሰዎች ያታልሉናል ቤተሰቦች ውሸትን ያምናሉ አሁን ልጆቻቸው በጣም አደገኛ ለሆኑ ሰዎች እየሰሩ ነው (በቀኝ በኩል ወዳሉት አመልክት) ልጆቹ አሁን ስለተጠመዱ በምንም ዓይነት ማምለጥ አይችሉም (በመሃል ቀኝና ግራ ወደ ቆሙት አመልክት) ብዙ ልጆች ለከባድ የጉልበት ሥራ በማሣና በዓሣ ማጥመጃ ጀልባዎች ተገድደው እንዲሰሩ ተደርገዋል፤ ከማለዳ ፀሐይ ወገግታ እስከ ማታ ግማሽ ሌሊት ድረስ ይሠራሉ፤ በቂ ምግብ ፤ ውሃ፤ የእንቅልፍ ወይም የእረፍት ጊዜ አያገኙም ፡ ፡ ለማረፍ ወይም ትንሽ ለመጫወት ቢሞክሩ ይደበደባሉ ሲከፋም ይገደላሉ (ወደ አልተነጠፈው አልጋና ወለል ላይ ወዳለው ልጅ አመልክት)
- ብዙ ልጆች ሌሊቱን እንዲሠሩ ይገደዳሉ ሰዎች የግብረ ስጋ ግንኙነት ሊፈጽሙባቸው ሲፈልጉ ለአሰሪዎቻቸው ይከፍላሉ ልጆች ተገድደው ይደፈራሉ፣ በአንድ ሌሊት አንዲት ሴት ልጅ ከ30 ሰዎች ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት እንድታደርግ ተደረጋለች (ከላይ ወዳለቺው ልጅ አመልክት)
- በዚህ ሁኔታ ልጅቷ ትሰበራለች ፡ በትንሽዬ ክፍል ተቆልፎባት መድኃኒት ተሰጥቷት ስለምትኖር ራሷን መከላከል እንዳትሞክር ትደረጋለች፡፡ በዚህ ሁኔታም ህይወት ማለት ይኸ መንገድ ብቻ መሆኑን በማመን ራሷንም ዋጋ የለሽ አድርጋ እንድታስብ ስለምትደረግ ራሷን በማስዋብ ለተሰጠችው ሰው አስደሳች መሆን እንዳለባት እንድታምን ትደረጋለች ሕይወት ዋጋ እንዳለው አታምን፡፡
- አንድ ሰው/መንግስታዊ አካል/ እነዚህን ህፃናት ካልረዳቸው በአስገድዶ መደፈር፣ በድካምና በበሽታ ይሞታሉ፡፡

## 7 ለልጆችና ለቤተሰቦቻቸው ተስፋ አለ



- (በግራ ጠርዝ ላይ ወደሚታዩት ቤተሰብ አመልክት) ከቤተሰብህ ጋር በጥብቅ ተያያዝ ማንም ገንዘብ ቢሰጥህ ከአንተ አርቀህ ለትምህርት ወይም ለሥራ ከሌላ ሰው ጋር አትላክ፣ ለጉዞአቸው እከፍላለሁ ከሚል ሰው ጋር አትላካቸው የራስህንም ሆነ የልጆችህን መታወቂያ ለማንም ሰው አትስጥ
- (ስልክ ወደያዘችው ሴት አመልክት) ከቤተሰቦቻቸው በጉልበትና በማታለል የተወሰዱ ልጆችን ብታይ ወይም ስለ እነርሱ ብትሰማ በአካበቢህ ወዳለ የህግ አካል ደውል የመንግስት አካላት /ባለስልጣናት / ተከታትለው የልጆቹን ደህንነት ሊያስጠብቁ ይችላሉና ነፃም ያወጡአቸዋል ለእንደነዚህ አይነት ሰዎች የእኛ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል፡፡
- በማነኛውም ጊዜ ብትጠለፍ ወይም በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ብትገባ በአቅራቢያህ የሚገኘውን ምልክት ሊሆን የሚችለውን ነገር አስተውል፡ በአካቢህ ላለ የህግ አካል ስልክ ደውል በማነኛውም ጊዜ ድጋፍ ጠይቅ የደወልኸውን ቁጥር ያነሱ ሰዎች ድጋፍ ሊሰጡ/ሽ/ ይችላሉ ከችግር ትተርፋለህ/ ትድናለህ
- ( ክፍት ወደሆነው ሰንሰለት አመልክት) ልጆቻቸው ብዙ ጊዜ ከጠላፊዎች እጅ ካመለጡ ወላጆች ኃፍረት ስለሚይዛቸውና ልጃቸውን የተጠቀሙበት ስለሚመስላቸው ደግሞም ታሞ ስለሚሆን የማይፈልጉት ይሆናል፡፡
- ( ክፍት ወደሆነው በር አመልክት) በዚህ በተከፈተው በር በኩል ቤተሰቡም ሆነ ልጁ ነፃነትና ፈውስ ያገኛሉ ትንሽ እንኳን ክፍት በር ተገኝቶ ልጁ ሊመለስ ቢችል ቤተሰቡ ከብዙ ጉዳቶቻቸው መፈወስ ይጀምራሉ
- ቤተሰቡ ቢሰበሩም ቢቆስሉም ያ የቆሰለው ልባቸውና የተሰበረው መንፈሳቸው ልጁ በመመለሱ ምክንያት መጠገንና መሙላት ይጀምራል፡፡

ስለዚህ ስለተከፈተ በር ሌላ ታሪክ እንድነግርህ ትወዳለህ ? ዋጋ የማይከፈልበት የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል በር ለሰው ሁሉ ተከፍቶአል ስለሆነም ማናችንም እርሱን ከሰማን ምንም ዋጋ መክፈል ሳያስፈልገን በክርስቶስ ኢየሱስ ነፃነትን፣ ፈውስንና ወደ ቀድሞ ማንነታችን መመለስ እንችላለን፡፡

## መረጃ

- በየ30 ሰኮንዱ አንድ ህፃን በአዘዋዋሪዎች እጅ ይወድቃል (ምንጭ:- ዩኒሴፍ)
- በአሜሪካን ሐገር በአማካይ ዕድሜአቸው 13 ዓመት የሆኑት ልጆች በዝሙት አዳሪነት ይሰማራሉ (ምንጭ:- የአሜሪካን ህግ አገልግሎት ክፍል)
- ከ192 የዓለም ሀገራት በ161 ውስጥ ህገወጥ የህጻናት ዝውውር ይካሄዳል ( ምንጭ:- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት)
- በዝሙት ከሚተዳደሩት ሴቶች 96% የሚሆኑቱ ከጉዳዩ ማምለጥ እየፈለጉ ግን እንደማይሆንላቸው ይሰማቸዋል ( ምንጭ :- የተባበሩት ሠራተኞች ድርጅት)
- ህገወጥ የሰዎች ዝውውር በዓመት 32 ቢሊዮን ዶላር የሚገኝበት ሥራ ነው ( ምንጭ :- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት)
- በአንዳንድ ሀገራት 70% የሚገመቱ ወንዶች ለግብረ ስጋ ግንኑነት ብር ከፍለው ይጠቀማሉ ( ምንጭ :- ቪክተር ማላረክ )
- በአሁኑ ሰዓት በዓለም ላይ ከ27 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች በባርነት ውስጥ የገቡ ሲሆን ይህ አሃዝ ደግሞ በትራንስ አትላንቲክ ዘመን ከነበረው የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ከተካሄደው እጥፍ በላይ ነው፡፡ ( ምንጭ :-ፍሪተ ዘ ስሌቭስ

## ምርጥ ተሞክሮዎች

### እንደ ድርጅት እና እኛም ደግሞ ድርጅቱን እንደወከል መጠን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆነን እነኝህን ነገሮች ማድረግ የለብንም፡፡

- ጥቂት የተበዘበዙ / ከችግሩ ያመለጡ/ ሕፃናት ፎቶዎችን ፊት አሳይ
- በችግሩ ውስጥ ተቋቁመው ያለፉትን ተጠቂዎች እውነተኛ ስም /ማንነት/ አካባቢ በሚገልጽ ሁኔታ አትተርክ
- በችግሩ የተጠቁትን አካላት / አሳዳጊዎቻቸውን ሳታስፈቅድ ታሪካቸው በማንኛውም መገናኛ ብዙኃን መንገድ አይገለጽ
- ችግሩን ባለማጋነንና ባለማሳነስ በታማኝነት ለሚመለከተው እናሳውቃለን
- ከችግሩ ሰለባ ተጋፍጠው ከተቋቋሙት አካላት ጋር ግንኙነት ያላቸው ፎቶዎችና ታሪኮች በማንኛውም መንገድ ከመታተማቸው በፊት በቡድኑ መሪ አማካይነት መወገድ ይኖርባቸዋል፤ ለምሳሌ:- በበራሪ ወረቀት፣ ድረገጽ፣ እና ሌሎችም ማህበራዊ ሚዲያዎች
- በመስክ ስራችን ወቅት ስለ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂ ስለሆኑት ወገኖች ጉዳይ ስንዘግብ ወይም መረጃዎችን ስንሰጥ ማለትም:- ስም፣ እድሜ፣ የተጠቂውን/ዋን / አድራሻና ሌሎች መግለጫዎችን ስናጠናክር ልንገነዘባቸው ከሚገቡን ሁኔታዎች ዋናው መረጃው በቡድን መሪአችን እጅ መግባቱንና በጥንቃቄ ተጠብቆ ችግሩን ለማስቆም ተገቢ እርምጃ ለመውሰድ ስራ ላይ መዋሉን ነው

## የድርጊት ደረጃዎች

- ጸሎት
  ኢየሱስ ምርኮኞችን ነፃ ሊያወጣ መጣ፤ ስለዚህ እኛ ከእርሱ ጋር መገናኘት፣ የኢየሱስን ዋና ዓላማ ማሳካትና ዘመናዊውን የሰው ልጅ ባርነት ቀንበር ልናጠፋ የምንችለው በዚህ ብቻ ነው
- ግንዛቤ
  ዊሊያም ዊለብረፎርስ የተባሉት ሰው ሲናገሩ:- ሁኔታዎችን በሌላ አቅጣጫ ልታያቸው ትችላለህ ነገር ግን አላውቀውም ልትል አትችልም፤ ምክንያቱም አሁን ተምረኸዋል ስለዚህ ልትደርሳቸው ለምትችላቸው ሰዎች ግንዛቤ በማስጨበጥ በቁርጠኝነት ጨክነህ ለነፃነት ታገል ከዚህም ባለፈ የተገነዘብኸውን ለምታውቃቸው 10 ሰዎች እና ለማታውቃቸው 10 ሰዎች በማከፈል የነፃነት ትግልህን ቀጥል፡፡
- መስጠት
  ገንዘብ ለህገወጥ የሰው ልጅ ዝውውር ወረርሺኝ ጀርባ ዋና ነጂ ኃይል ሲሆን ይህንንም ልንታገለው ይገባል፤ ስለዚህ ህገወጥ የሰው ልጅ ዝውውርን የሚቃወሙና የሚታገሉ ድርጅቶችን በእውነተኛ መሰጠት እና ገንዘብንም በመስጠት ልትደግፋቸው ይገባል፡፡

## የአካባቢ ሆት ላይን ቁጥር